# ሰቆቃወ ጴጥሮስ

አየ፥ ምነው እመ ብርሃን? ኢትዮጵያን ጨከንሽባት?
ምነው ቀኝሽን ረሳሽት?
እስከመቼ ድረስ እንዲህ፥ መቀነትሽን ታጠብቂባት?
ልቦናሽን ታዞሪባት?
ፈተናዋን፥ ሰቀቀንዋን፥ጣሯን ይበቃል ሳትያት?
አላንቺ እኮ ማንም የላት....
አውሮጳ እንደሁ ትናጋዋን፥ በፋሽስታዊ ነቀርሳ
ታርሳ፥ተምሳ፥ በስብሳ
ሂትለራዊ እባጭ ጫንቃዋን፥ እንደ ኮረብታ ተጭኗት
ቀና ብላ እውነት እንዳታይ፥ አንገቷን ቁልቁል ጠምዝዟት
ነፍሷን ድጦ ያስበረከካት
ሥልጡን ብኩን መፃጉዕ ናት፤....
እና፥ ፈርቼ እንዳልባክን፥ ሲርቀኝ የኃይልሽ ውጋጋን
አንቺ ካጠገቤ አትራቂ፥ በርታ በይኝ እመ ብርሃን
ቃል ኪዳኔን እንዳልረሳት፥ እንዳልዘነጋት ኢትዮጵያን።
አዎን፥ብቻዬን ነኝ ፈራሁ
እሸሸግበት ጥግ አጣሁ
እምፀናበት ልብ አጣሁ፥
እማማ ኢትዮጵያን መንፈሴ፥ተፈትቶ እንዳይከዳት ሠጋሁ..
አዋጅ፥ የምሥራች ብዬ፥የትብት ምግቤን ገድፌ
ከናቴ ማህፀን አልፌ
በኢትዮጵያ ማህፀን አርፌ፥
ከአፈርዋ አጥንቴን ቀፍፌ
ደሜን ከደሟ አጠንፍፌ
ከወዟ ወዜን ቀፍፌ
በሕፃን እግሬ ድኼባት፥በሕልም አክናፌ ከንፌ
እረኝነቴን በሰብሏ፥ በምድሯ ላብ አሳልፌ
ከጫጩትና ከጥጃ፥ከግልገል ጋር ተቃቅፌ፤
በጋው የእረኛ አደባባይ፥ ክረምት እንደወንዙ ፍሳሽ
በገጠር የደመና ዳስ፥ በገደል ሸለቆ አዳራሽ
ከቆቅና ከሚዳቋ፥ከዥግራ ጠረን ስተሻሽ
በወንዝ አፋፍ ሐረግ ዝላይ፥ መወርወር መንጠልጠል ጢሎሽ
ከፍልፈል ጋር ሩጫ ስገጥም፥ ከቀበሮ ድብብቆሽ
ከናዳ ጫፍ ሳር አጨዳ፥ለግት ላሜ ትንሽ ግጦሽ
ለጥጃዬ የሴት ግርዶሽ
ለጥማድ በሬዎች ራት፥ ለማታቸው ትንሽ ድርቆሽ
ለግልገሌ ካውሬ ከለል
እማሳው ሥር ጎጆ መትከል
ለፀሐይ የሾላ ጠለል፥ ለዝናብ የገሳ ጠለል
ውሎ የንብ ቀፎ ማሰስ፥ ያበባ እምቡጥ ሲፈነዳ
ግጦሽ ሣር ሲለመልም፥ ሲሰማሩ ሰደድ ሜዳ
አዝመራው ጣል ከንበር ሲል፥ ከብቱ ለሆራ ሲነዳ
ፈረስ ግልቢያ ስሽመጥጥ፥ ከወፎች ዜማ ስቀዳ
ልቤ በንፋስ ተንሳፎ፥ በዋሽንት ዋይታ ሲከዳ...
ያቺን ነው ኢትዮጵያ የምላት
እመ ብርሃን እረሳሻት?
ያችን የልጅነት ምሥራች? የሕፃንነት ብሥራት
የሣቅ የፍንደቃ ዘመን፥ የምኞት የተስፋ ብፅአት
ያቺን የልጅነት እናት?
አዛኚቱ እንዴት ብለሽ፥ ጥርሶችሽን ትነክሽባት?
ስሜን በስምሽ ሰይሜ፥ባገልግሎትሽ ስዋትት
ከዜማ ቤት እቅኔ ቤት፥ ከድጓ ቤት እመፅሐፍት
ካንቺ ተቆራኝታ ዕድሌ፥ ካንቺ ተቆራኝታ ነፍሴ
ከቀፈሩ ደጆ ሰላም፥ ከቤተ ልሔም ቅዳሴ

www.ethiopianorthodox.org

እኮ÷ ቀፎ÷ ዳባ ለብሶ
ቅኔ ዘርፎ ግሥ ገሦ
መቅደስ አጥኖ÷ማኅሌት ቆሞ
በልብሰ ተክህኖ አጊጦ÷በብር አክሊል ተሸልሞ
እመ ብርሃን ያንቺ ጽላት÷ ነፍሴ ላይ በሳት ታትሞ
የመናኒው ያባ ተድላ÷ ረድ ሆኜ አብሮኝ ታድሞ
ሕይወቱ እምነትሽን ጸንሶ
ሥጋ ፈቃዱ ተድሶ
ለሕንፃሽ መዲና ቆሞ÷ ለክብርሽ ድባብ ምሰሶ፤
ስሜን በስምሽ ሰይሜ÷ ሆነሽኝ የእምነቴ ፋኖስ
ለዋዜማሽ ግሽን ማርያም÷ ለክብርሽ ደብረ ሊባኖስ
ስሮጥ÷ በወንበሩ አኖርሺኝ÷ በአንበሳው በቅዱስ ማርቆስ
ታዲያን ዛሬ ኢትዮጵያ ስትወድቅ÷ ከምትሰጪኝ ለፍርሃት ጦስ
ምነው በረኝነት ዕድሜ÷ ዓይኔን በንጎጣት የሎስ
የጋኔል ጥንብ አንሳ ከንፎ÷ ወርዶ በጨለማ በርኖስ፡፡
ባክሽ እመብርሃን ይብቃሽ÷ ባክሽ ምስለ ፍቁር ወልዳ
ጽናት ስጪኝ እንድካፈል÷ የእናቴን የኢትዮጵያን ፍዳ
ከነከሳት መርዝ እንድቀምስ÷ ከነደደችበት እቶን
የሷን ሞት እኔ እንድሞታት÷ ገላዋ ገላዬ እንዲሆን፡፡...
አዎን÷ ብቻዬን ነኝ ፈራሁ
እምፀናበት ልብ አጣሁ፡፡...
ሕፃን ሆኜ የእርግብ ጫጩት÷ አንዳንዴ ራብ ሲያዳክማት
ችጋር ከጎጆዋ ገፍቶ÷ እዛፍ ግርጌ ሲጥላት
እናቷ በርራ ደርሳላት
በአክናፏ ሙቀት ታቅፋት
እፍ እያለች ግንባሯ ላይ÷ ሕይወት ስትተነፍስባት
ወዲያው ነፍስ ትዘራለች
ሽር-ብር-ትር እያለች፡፡
ባክሽ አንቺም አትራቂብኝ
እመ ብርሃን እናቴ÷ ትንፋሽሽን እፍ በይብኝ
ፅናትሽን እፍ በይብኝ÷
ወይም ይቺን የሞት ጽዋ÷ ጥላዋ ነፍሴን ካፈናት
እንዳልጠጣት አሳልፊያት
መራራ ክንፏን ገንጥለሽ÷ቀጠሮ÷ቃልዋን ግደፊያት፤...
አለዚያም ፅናትሽን ስጪኝ÷ ልጠጣው ኪዳኑ-ውሉን
የኔ ፍቃድ እምነትሽ ነው÷ ያንቺ ፍቃድ ብቻ ይሁን፡፡
እንደ ጳውሎስ እንድፀና÷በፍርሀት እንዳልታሰር
በውስጤ ከሚታገለኝ÷በሥጋ አውሬ እንዳልታወር
ለዕየሉቱ ሞት እንዳልሰንፍ
የኪዳኔ ቃል እንዳይነጥፍ
ቃልሽ በሕሊናዬ ዲብ ÷ኃይልሽ በህዋሴ ይረፍ፡፡
ፍርሀት ቢያረብብኝም ÷አንቺ ካለሽ አልሰጋም
ኩርትም ብዬ እችልበት ÷እሸሸግበት አይጠፋም
የግማደ መስቀሌን ጉጥ ÷ እታገስበት አላጣም
አለዚያማ ብቻዬን ነኝ÷ኢትዮጵያም አላንቺ የላት
አንቺ አዕኛኝ  እንድጸናላት፡፡
አስርጪብኝ የእምነት ቀንጃ÷ለሥጋቴ አጣማጅ አቻ
ለጭንቀቴ-መቀነቻ፡፡.......
አዎን÷ ብቻዬን ነኝ ፈራሁ
እሸሸግበት ጥግ አጣሁ
እምፀናበት ልብ አጣሁ.....
፲፱፻፺፩ ቀበና (ፀጋዬ ገብረ መድህን)

www.ethiopianorthodox.org